በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

ሕዳር 10ቀን 2006 ዓ.ም

የተሰጠ መግለጫ

**መብትን ማስከበር የሚቻለው ተደራጅቶ በመታገል ብቻ ነው።**

የወያኔ/ኢህአዴግ የጭቆናና የአፈና አገዛዝ ከንዱን ካሣረፈባቸው ማህበራት አንደኛውና ቀዳሚው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ነው። ኢመማ በዚህ ሥርዓት የሚደርስበት ውርጅብኝ መንስኤው ለአባላቱ መብትና ጥቅም መከበር፣ ለትምህርት ጥራትና በዕኩልነት መዳረስ ፤ለፍትሕና መልካም አስተዳደር መስፈን እየታገለ በጽናት መቆሙ ነው። ኢመማ ለዚህ ዓላማና ግብ ጸንቶ በመቆሙ ወያኔ አንዴ በተቀዋሚ ድርጅቶች መሣሪያነት ፣ በሌላ ጊዜ የሕገወጥ ድርጅቶች ተባባሪ የሚሉ ያለተገባሩ ተግባር ፣ ያለስሙ ስም በመለጠፍ በሕግ ሽፋን በራሱ አሻንጉሊት ፍ/ቤትና አስመሳይ ዳኞች ውሳኔ ማህበሩን አፍርሶ በአምሳሉ የጠፈጠፈውን ተለጣፊ ማህበር አቋቁሟል። ይህን በካድሬ መምህራን የተሞላ ስብስብ ይዞ በመምህራን ላይ የአሻውን ሕገወጥ ተግባር ለመፈጸም አመቻችቷል።መጠነ ሰፊ ወንጀሎችንም ፈጽሟል፤እየፈጸመም ነው።

ይህ መሠሪ የሆነ በመንግሥት ስም የተዋቀረ ብልሹ ሥርዓት በነፃ የመደራጀት መብትን ጦር ካወጃ የውጪ ኃይል በበለጠ ይፈራል። ከሁሉም በላይ የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶም አፍራሽ ተልእኮዉን ያሳካል። በዓለም ድንጋጌዎችም ሆኑ በይስሙላው የአገሪቱ ሕገመንግስት ተብዬው የወያኔ ሰነድ ላይ የተካተተውን የመደራጀት ነፃነት ተገስሷል። ይህ ሁኔታ ለመምህራን የሙያ ክብር ጥያቄ ፣ የጥቅም ማስከበር ጥያቄ ፣ የመደራጀት ጥያቄ ፤---ከመሆን ባለፈ ራዕይ ያለው ትዉልድ የመተካት ሁለገብ ተግባር ለአደጋ የተጋለጠበትን ከስተት የመለወጥ ጥያቄ ሆኗል።

በታሪክ አጋጣሚ በኢትዮጵያ በሥልጣን እርካብ የተቆናጠጡ ገዢ ኃይሎች ሁሉ ሕዝብ የሚያነሳቸውን የመብት ጥያቄዎች በማዳመጥ በበጎ መልኩ ሲጠቀሙበት አልታየም። ይልቁንስ የራሳቸውን የፖለቲካና የሥልጣን ጥማት በማስቀደም ዜጎችን ለርሃብ ፣ ለድንቁርና ፣ ለሰደትና ውርደት ፣ አገሪቱን ለውድቀት ዳርገዋል።በተለይ በዚህ በአለንበት ወቅት በኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት መውደቅ ፣ የትምህርት ቤቶች ከሕዝብ ቁጥርና ዕድገት አለመጣጣም ፣ ለማስተማር መማር ስኬታማነት ምቹ አለመሆናቸው፣ ለተማሩ ዜጎች ከበሬታ መንፈግ ፣ ኑሮን ያለጭንቀት ለመምራት የሚያስችል ምንዳ በመከፈል የመንግሥት እንክብካቤ ማጣት ተስፋ አስቆራጭ ደረጃ ላይ መድረሱ በአገሪቱ ሰላም ፤ልማትና ዕድገት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ አስከትሏል። በዚህ ሂደት በተለይ የትምህርቱ ጉዳይ በከፋ ደረጃ መውደቁንና በሙያው በተሰማሩ መምህራን ላይ እየደረሰ ያለውን ዙሪያ ገብ አሉታዊ ተግባር ቀጥሎ ባሉት አንቀጾች በማሳያነት እናቀርባለን።

አገሪቱ የምትፈልገዉን የሰው ኃይል የሚቀርጸው መምህር በኑሮው መጎሳቆሉ አልበቃ ብሎ ለአገሪቱ የሚያስፈልገውን ተማሪ አላበቃህም፣ የደጋሚና የአቋራጭ ተማሪ ዜሮ አላደረግህም፣ የትምህርቱን ጥራት ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ አላደረከም፣ ማንኛውም ተማሪ 50% እና ከዚያ በላይ ውጤት እንዲያመጣ አቅምህን አሟጠህ አላስተማርከም ፣ አንድ ለአምስት የፖለቲካ አደረጃጀትን ተግባራዊ በማድረግ የትምህርት የልማት ሠራዊት አልገነባህም፣ ራስህንም የልማት ሠራዊት አላደረግከም፣------በማለት የወያኔ ፓርቲ ካድሬዎች በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ህሊናውን ያቆስሉታል፤ የአካዳሚክ ነፃነቱንም ይገፉታል። በአጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታዎች ሲገመገሙ ሱሪ ባንገት አውጡ ዓይነት ነው።



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

በነገራችን ላይ መስከረም ሲጠባ እንደቀደሙት ዘመናት ተማሪዎችና አስተማሪዎች ተነፋፍቀው በአዲስ ዓመት ፣ በአዲስ መንፈስ ለማስተማር መማር ሥራ ይሠማራሉ የሚባልበት ተስፋ ጨልሟል ። መስከረም 3 ትምህርት ቤቶች ሲከፈቱ ትንሽ ቆሎ ይዞ ወደ አሻሮ ይጠጓል እንዲሉ ለይምሳል የትምህርት አጀንዳ ተሰንቅሮ ይቀርባል እንጂ አመዛኙ ጉዳይ የፖለቲካ ፕሮግራም ማራመድ ሆኖ የትምህርት ሽፋን ( ፖርሽን) የሚጎዳበት አሠራር ነው እየታየ ያለው። በዘንድሮ የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ወቅት በመንግሥት የቀረበው የሃይማኖት አክራሪነት የተሰኘው ሰነድ አንዱ ማሳያ ነው።በዚህ ሰነድም አክራሪነት ከተስፋ መቁረጥ ጋር ተያይዞ የከሰሩ ፖለቲካኞች የሚያራምዱት ከእውነተኛ የሃይማኖት ጥያቄ ጋር የተያያዘ እንዳልሆነና በሰላማዊ ትግል አማራጭ ከጨዋታ የወጡ ኃይማኖትን ተገን አድርገው ሥልጣን በአቋራጭ ለመያዝ የሚንቀሳቀሱ ኒዮ ሌበራል አቀንቃኞች የሚያደራጁት አደጋ ነው በማለት የወያኔ ካድሬዎች ላቀረቡት ሰፊ ገለጻ መምህራን በአገራችን የሃይማኖት አክራሪነት የለም፤ ይልቁንስ ጎልቶ የሚታየው የፖለቲካና የመንግሥት አክራሪነትና አሸባሪነት ነው በማለት ገልጸዋል። መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባቱን በአንክሮ ከመግለጻቸውም በላይ ሙስሊም ወገኖቻችን ያቀረቡት የመብት ጥያቄ ሕጋዊና ትክክለኛ ስለሆነ ፍትሐዊ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል ብለዋል።እንዲሁም መንግሥት በእስልምናና በክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል ግጭት ለመፍጠር በአንድ በኩል ሙስሊሞች የሸሪአ ሕግ ሊያውጁ ነው፤ የእስልምና መንግሥት ሊያቋቁሙ ነው ፤ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ የክርስትና ደሴት ናት፤ አንድ ሃይማኖት ፣ አንድ ጥምቀት ፣ አንድ አገር የሚሉ የኦርቶዶክስ ዕምነት አክራሪዎችም ብቅ ብቅ እያሉ ነው በማለት ካድሬዎች ለሰጡት ገለጻ መምህራን ተገቢውን የአጸፋ መልስ በመስጠት ሐሳቡን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርገውታል።

ሌላው ትምህርቱንና መምህራንን በቀጥታ የሚመለከተው ጉዳይ ከላይ ከቀረበው ጋር ተያይዞ በዚህ ዓመት መስከረም ወር 2006ዓ.ም በተደረገው አገር አቀፍ የመምህራን ስብሰባ የ2006ዓ.ም ዋነኛ ግብ ተደርጎ የተያዘው የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች በ 3 ወራት ጊዜ ውስጥ መጻፍና ማንበብ እናስችላለን ብላችሁ ቃል ግቡ የሚል በአንደኛ ደረጃ መምህራን ላይ ለመጣል የታቀደው ግዴታ ነው። መምህራን ግን በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ በሚማሩበት ፣ የትምህርት ዕቃዎችና ሌሎች መርጃ መሳሪያዎች ባልተሟሉበት ፣ ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች በአንድ መምህር እንዲማሩ በተደረገበት ፣ የመምህሩ የኑሮ ሁኔታ ባልተሻሻለበት ፣ መምህሩ ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች ለማስተማር የሚያስችል ሥልጠና ባልተሰጠበትና በተለይ የሥልጠና ፖሊሲው የችግሩ ዋና መንስኤ መሆኑ እየታወቀ በሶስት ወራት መጻፍና ማንበብ እናስችላለን ብሎ ቃል መግባት ፈጽሞ የሚታሰብና ሊሆን የማይችል በመሆኑ ዋና ዓላማውም መምህሩን ተጠያቂ ለማድረግ የተወጠነ ሴራ ነው በማለት የተቃውሞ ድምጻቸውን አሰምተዋል። በሌሎች በኢኮኖሚ በዳበሩ አገሮች መምህራን በአንድ ክፍል ውስጥ ሆነው ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች በተለይ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያስታምራሉ።ያ የሚሆነውም እያንዳንዱ መምህር ለሚያስተምርበት የክፍል ደረጃ በሚያስተምሩበት በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ስልጠና ተሰጥቶና ክፍሎቻቸውም ለሁሉም የትምህርት ዓይነት በሚያስፈልጉት የትምህርት እቃዎች ተሞልተው ነው። በጀትም ተመድቦ ነው ። በኢትዮጵያ ይህ ሁኔታ ሳይሟላ አንድ መምህር ሁሉንም ትምህርት እንዲያስተምር መደረጉ በትምህርት ላይ የሚፈጸም የትውልድ ግድያ አንዱ ዘዴ ነው።

ከተማሪዎች ውጤት መሻሻል በተያያዘ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች 15% የሚሆኑ ተማሪዎች 85% እና ከዚያ በላይ ውጤት ፣ 35% የሚሆኑ ተማሪዎች 75% እና ከዚያ በላይ ፣ 50% የሚሆኑ ተማሪዎች 50% እና ከዚያ በላይ ውጤት እንዲያመጡ በእቅድ ይዛችሁ መስራት ይኖርባችኋል ። አንድም ተማሪ ከ50% በታች ውጤት ማምጣት የለበትም የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ተላልፏል። ይህም የወያኔ መንግሥት የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብ ለማሳካት ይሄለሁ ከሚለው እቅድ አንፃር ተማሪዎች ለክፍል ደረጃቸው የሚመጥናቸውን ዕውቀት ሳይጨብጡ መምህራን ወደሚቀጥለው ክፍል እንድያሳልፏቸው ለማድረግ የታሰበ የትምህርቱን ጥራት ያመከነ አንደኛው ሴራ ነው። ለዚህም ማሳያ ሊሆን የሚችለው በወርሃ ሰኔ 2005 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል( ከ1ኛ-4ኛ ክፍሎች)በትምህርት ያገኙት ውጤት ዝቅተኛ በመሆኑ እንዲደግሙ የተደረጉ ተማሪዎች ውጤቱ ተሰርዞ የማለፊያ ማርክ መምህራን ሰጥተው እንዲያሳልፉ ተገደዋል። እንዲሁም በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች እስከ ከፍተኛው የትምህርት ተቋም ዩኒቨርሲቲ ድረስ ለተማሪዎች " F " የሰጡ መምህራን የትምህርት ዕድልመነገፍና ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች ላይ የመካፈል መብት ተነፍገዋል። ይህ አሠራር ለትምህርት ጥራት መቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ የመምህራንን በነፃነት የመሥራትና የመወሰን መብት የጣሰ፣ የፓርቲ ትዕዛዝ ፈጻሚ እንጂ የህሊና ዳኝነት ፣ የመርሕም ሆነ አገራዊ ራዕይ ዋጋ የማይሰጠው በመሆኑ ከፍተኛ ተቃውሞ ከመምህራን አስነስቷል።

*ይህ በእንዲህ እንዳለ በዚሁ በ2006 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የመምህራን ስብሰባ ለተነሳው ጥያቄ ለመምህራን የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ አድርገናል፤ በየዓመቱ የጎንዮሽ የደመወዝ ጭማሪ ይደረጋል በማለት በመጋቢት ወር 2004 ዓ.ም በሬዲዮና ቴሌቪዥን የቀረበው ድስኩር መሳይ ፕሮፖጋንዳ የውሃ ሽታ ሆኖ ከመቅረቱም በላይ ይህን አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ለመስጠት የተቸገሩ ሲሆን የአዲስ አበባው የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ግን ጉዳዩን አዲስ በማድረግ አዲስ የደመወዝ ጭማሪ በመንግሥት እየተጠና መሆኑን ለማስረደት ሞክረዋል። በሌሎች መስሪያ ቤቶች ለሚሰሩ ሰራተኞች ለምሳሌ ለንግድ ባንክ ሰራተኞች እስከ 100% ፣ በሕግ ሽፋን ለሥርዓቱ ጉዳይ አስፈጻሚ ለሆኑት ለፍትሕ አካላት የደመወዝ ጭማሪ ሲደረግላቸው ለቴሌ ሠራተኞችም እስከ 15,000 ( አስራ አምስት ሺ ብር) እና ከዚያ በላይ ድጎማ ( ቦነስ) ተሰጥቷል። ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞችም በመዋቅር ለውጥ ስም ከፍተኛ የደመወዝ ጭማሪ ለማድረግ ዝግጅት ያጠናቀቁ መሆኑ እየታወቀ የመምህራን የደመውዝ ጭማሪ ገና በመንግሥት እየተጠና መባሉ ለመምህራንና ለሙያው ያላውን ንቀትና ዝቅተኛ አመለካከት የሚያሳይ ነው። ይህም አልበቃ ብሎ ከእጅ ወደአፍ በሆነ ገቢ ኑሮውን የሚገፋውን መምህር ፈቃዳኝነቱ ሳይጠየቅ በማን አለብኝነት ገንዘቡን ይነጥቁታል። ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው በአንዳንድ አካባቢዎች መምህራን በመስሪያ ቤታቸው ይከፈላቸው የነበረው ደመወዝ በንግድ ባንክ በኩል ለባንኩ የአገልግሎት ክፍያ 5 ብር በየወሩ ከእያንዳንዱ መምህር ደመወዝ እየተቀነሰ የሚከፈልበት መመሪያ አስተላልፋዋል። በተወሰኑ ት/ቤቶችና ቅርንጫፍ ንግድ ባንኮች የተደረገው የደብዳቤ ልውውጦችም በእጃችን ገብቷል። ይህ መመሪያ በመምህራን ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል። ስለሆነም መምህራን በሁሉም አካባቢ በትምህርት ጽ/ቤቶች ሠራተኞች የደመወዝ ክፍያ አገልግሎት ዘርፍ ደመወዛቸው ይከፈላቸው እንደነበረና ይህ አሠራር ወደ ባንክ ተዛውሮ ለተጫማሪ ወጪ መዳረጋቸው አግባብነት እንደሌለው ስምና ፊርማቸውን በማስፈር( ፔቲሽን በማሳባሰብ) ምሬታቸውን በመግለጽ ላይ ይገኛሉ።*

*በሌላ በኩል ደግሞ በጎፋ አካባቢ ባሉ ከአራት በማያንሱ ት/ቤቶች በማስተማር ሙያ የተሰማሩ መምህራን ለአባይ ግድብ በሚል የወር ደመወዛቸው ያለፈቃዳቸው በመቀነሱ ለተወሰነ ጊዜ የስራ ማቆም አድማ መተው እንደነበር ይታወቃል። በሀድያና ከምባታ ዞኖችም 23 መምህራን ከሚያስተምሩበት ት/ቤት ያለጥያቄያቸው እንዲዛወሩ ተወስኖባቸው የነበረው በሁሉም ቦታ በተካሄደ የመምህራን ተቃውሞ ዝውውሩ ከሽፏል ።*

*ወያኔ/ኢ.ህአዴግ የመምህራን ሞራል በግምገማና በደረጃ ዘይቤ እንዲጎዳ አድርጓል። መምህራን በነፃ ተደራጅተው መብትና ጥቅማቸውን ማስከበር እንዳይችሉ ተደርጓል። የአካዳሚክ ነፃነታቸውም ተገፏል።ከዕለት ወደዕለት ተነሳሽነትን በሚገድል ሁኔታ የፓርቲ ተሿሚ ካድሬዎችና ርዕሳነ መምህራን የማን አለብኝነት ርምጃ ሰለባ ሆነው አፈናው ቀጥሏል። በዚህ የተነሳ አያሌ በልምድ የዳበረ የማስተማር ሙያ ያላቸው መምህራን ሥራቸውን ለመልቀቅ ተገደዋል ፣ተባረዋል፣ ተፈናቅለዋል። አዲስ ተቀጣሪ መምህራንም አስከፊውን ሁኔታ በማየት ሥራውን ለዘለቄታ ሳይሆን መሸጋገሪያ አድርገዋል። የባሳውና አሳዛኙ ከስተት ደግሞ መምህራን ከሙያቸው ሥነምግባር ውጪ እንዲሰሩ ለመብትና ጥቅማቸው እንዳይታገሉና ለሙያቸው ጥብቅና እንዳይቆሙ ለማድረግ ለያይቶ መምታት በሚለው የከፋፍለህ ግዛ ስልት መጠቀማቸው ነው ። ይህን ዕኩይ ተግባር ለማስፈጸም መሣሪያ ሆነው የሚያገለግሉት ደግሞ ለመምህሩ ውርደትና ውድቀት መፋጠን የቆሙ የተለጣፊው መምህራን ማህበር አመራር ነን ባዮች ናቸው። እንዲያው መምህራን እረኛ የሌለው መንጋ ያህል ለአራዊት ሥርዓት ተጋልጠዋል። በመምህራን ላይ እየደረሰ ያለው ሰቆቃ ዙሪያ ገብ ነው የምንለው ከዚህ በመነሳት ነው። ይህ በዚህ እንዳለ አሁንም ለመምህራን ቀኑ የጨለመ አይደለም ። ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ በየቦታው የታየው እምቢተኛነት እንኳ በራሱ ለሥርዓቱ ሎሌዎች የማስጠንቀቂያ ደወል እንደሆነ አመላክቷል። ችግሩ እነዚህን በየቦታው የሚታዩ የትግል ብልጭታዎች ማቀናጀትና ብሔራዊ ቅርጽ አሲዞ ማስቀጠል ላይ ነው ። ለዚህም ደግሞ መደራጀት ዋነኛው መሣሪያ እንደሆነ ይታመናል። ወገኖቻችንን ከጭቆና አገዛዝ ለማላቀቅ በመታገል አኩሪ ታሪክ ያላቸው መምህራን ራሳቸውን ከጥቃት መከላከል የማይችሉ ምርኮኛ ሠራዊት ተደርገው ሲቀለድባቸው ማየት የታሪክ ጠባሳ ከመሆኑ ባሻገር ሙያዊና ብሔራዊ ግዴታንም ባለመወጣት በተተኪው ትውልድ በተጠያቂነት ያቆማል። ተደራጅተን ከመሰል ሲቪል ማሕበራት ጋር በመቀናጀት ትግልን አጧጡፎ ለዘላቂ ድልና ለሕዝባዊ ሥርዓት ምሥረታ የበኩልን መወጣት በእጅጉ ይጠበቅብናል።*

*ሰው ማህበራዊ ፍጡር በመሆኑ ኑሮውን የሚመራው እርስ በርስ በመደጋገፍና በመተጋገዝ ነው ። በማህበር በመደራጀት ነው። ድርጅት ኃይል ነው። ድርጅት የትግል መሳሪያ ነው። መምህራን በወያኔ መንግሥት የሚደርስባቸውን ከላይ የተዘረዘሩትን ዘርፈ ብዙ ጥቃቶችን ለማስወገድና መብትን ለማስከበር በስልት መደራጀት ተደራጅቶም መታገል ብቻ ነው መፍትሔው ብሎ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አስተባባሪ ኮሚቴ ያምናል። በአገራችን ውስጥ በመንግስት ሥልጣን የሚገኘው ቡድን መምህራንንም ሆነ ሌላውን የሕብረተሰብ ክፍል በጉልበት፣ በማስፈራረትና በመከፋፋል በሥልጣን ላይ ለመቆየት ቆርጦ የሚሰራ ኃይል በመሆኑ መምህራንም ሆኑ አጠቃላይ ህብረተሰቡ ፍርሃትን በማስወገድ በህብረት በመታገል ለድል እንዲበቁ በስደት የኢትዮጵያ መምህራ ማሕበር አስተባባሪ ኮሚቴ በድጋሚ ጥሪ ያደርጋል።*

*መደራጀት የወቅቱ ጥያቄ ነው!!*

*ኢመማ ለድርጅታዊ ጥንካሬ ተግቶ ይሠራል !!*

*የሲቪል ማሕበራት መጠናከር ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ምሶሶ ነው!!*

*ሲቪል ማሕበራት ያብቡ!!!*